የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/1532/14
ቀን/Date 06 ግንቦት 2014

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ:- <u>የመሠረታዊ ሸቀጦች የፍራንኮቫሉታ አገልግሎት እና የቀረጥና ታክስ ውሳኔን ይመለከታል</u>፤

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/5302 ቀን 30/7/2014 በተጻፈ ደብዳቤ በውጭ አገር የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች የሆኑት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የህጻናት ዱቄት ወተት እና ሩዝ ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ (በፍራንኮቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እየተፈቀደ እንዲገባ በመንግስት መወሰኑን፤ እንዲሁም በቁጥር ማኢ.30/7/5340 ቀን 06/08/2014 በተጻፈ ደብዳቤ የመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦቹ የቀረጥና ታክስ በተመለከተ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቁጥር ማኢ.30/7/1431 ቀን 28/12/2013 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም ማሳወቁን ተከትሎ ከኮሚሽኑ በቁጥር 4/1476/14 ሚያዚያ 04 ቀን 2014 እንዲሁም በቁጥር 4/1482/14 ሚያዚያ 07 ቀን 2014 በተጻፉ ደብዳቤዎች ለአፈጻጸም መተላለፉ ይታወሳል።

ሆኖም ቀደም ሲል ከኮሚሽኑ ለአፈጻጸም ከተላለፉት ደብዳቤዎች ጋር ተያይዞ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ስለመሆኑ እየተስተዋለ በመሆኑ ቀደም ሲል ከኮሚሽኑ የተላለፉት ደብዳቤዎች ተሰርዘው:-

1. የገንዘብ ሚኒስቴር በወሰነው መሠረት አስመጪዎቹ በውጭ ሀገር የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ስለመሆናቸው በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት በኩል የተረጋገጠ ደብዳቤ፤
2. አስመጪዎቹ በዘርፉ የታደሰ የአስመጪነት ፈቃድ ያላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የአስመጪነት ንግድ ፈቃድ በቀጥታ ለሚስተናገዱበት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሲያቀርቡ፤

ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ፈጽመው የምግብ ሸቀጦቹን ወደ ሀገር እንዲያስገቡ፤ እንዲሁም ቀደም ሲል አስመጪዎቹ የራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ያላቸው ስለመሆኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በኩል ተረጋግጦ የምግብ ሸቀጦቹን በፍራንኮቫሉታ ወደ ሀገር እንዲያስገቡ ከኮሚሽኑ በደብዳቤ የተገለፀላቸው አስመጪዎች ተጨማሪ ደብዳቤ ማቅረብ ሳይጠበቅባቸው ቀደም ሲል በተፈቀደላቸው አግባብ እንዲስተናገዱ እንዲደረግ እና አፈጻጸሙን በየወሩ አባሪ በተደረገው ቅጽ መሠረት ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እንድታቀርቡ፤ ዳይሬክቶሬቱም መረጃውን በማደራጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት እንዲያቀርብ እያሳሰብኩ፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ያስተላለፈውን ውሳኔ 03 ገጽ እና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ 01 ገጽ በድምሩ 04 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፤</u>
- ለኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢፌዴሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት

<u>አዲስ አበባ</u>

ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር እንዲሰፍን ተግተን እንሰራለን
ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባና ስሪት ሀገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለአቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>፣

